# ከበርማ እስከ ታይላንድ እስከ ምእራብ አፍሪካ -- ለሐበሻ ፖለቲከኞች ትምህርት

ከገመቹ ተካልኝ

የሀገራችን ፖለቲከኞች ሲደመጡ በወያኔ ምርጫ ከመካፈል ውጪ ምንም ሌላ አማራጭ የለም ሊሉ ይከጅላችዋል። በምርጫ አለመካፈል ለወያኔ መሸነፍ ነው ሲሉም ተሰምተዋል። ይህ ግን የተሳሳተ አቅዋም ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለም። የወያኔ ምርጫ ከወዲሁ ለወያኔ አሸናፊነት ተመቻችቶ የሚገኝ ነው። የምርጫው ህግና ቦርድ በወያኔ ቁጥጥር ስር ናቸው። በ 1997 እንደታየው ወያኔ ከተሸነፈም ህዝብ ፈጅቶ ወደ ስልጣን ይመለሳል። (በነገራችን ላይ ዛሬ 50 ዓመት ሞላው ተብሎ በሚከበረው የደቡብ አፍሪካ የሻርፕቪል ፍጅት ተገደሉ የተባሉት 122 አፍሪካኖች ሲሆኑ አረመኔው ወያኔ በ1997 በአዲስ አበባ ብቻ ከ 200 ያላነሱ ንጹህ ዜጎችን ፈጅቷል) ።

ከወያኔ ጋር በምርጫ ከመሰለፍ ባሻገር የህዝብ ትግል ብዙ ሌላ አማራጭ አለው። የበርማዋን የፖለቲካ ታጋይ ኣንግ ሳን ሱ ኪ በየጊዜው የሀገራችን ፖለቲከኞች ሲያነሷት አድምጠናል። አንግ ሳን ሱ ኪ በቁም እስር ካለችበት ቦታ ትላንት ወዲያ በጠበቃዋ አማካይነት ባስተላላፈችው መልእክት <u>ድርጅቷ በምርጫ እንዳይሳተፍ</u> ነግራለች። ይህን ያልችበትም ምክንያት የሀገሯ የበርማ የምርጫ ህግ ያልተቀየረ በምሆኑ ነው። ይህን ትክክለኛ አቅዋም ከኛዎቹ ጋር ስናወዳድረው የምርጫው ህግና ቦርድ ባልተለወጡበት መሳተፍ ብቻ ሳይሆን በእስር ያለችው የድርጅት መሪ ባትፈታም ምርጫ እንገባለን ብለው ለውድድር እነሆ ቀርበዋል። ወይዘሪት ብርቱካንን ከአንግ ሱን ኪ ማመሳሰል ፈላጊ የሆኑት ክፍሎች የሳንሱኪንም አቅዋም ቢከተሉ ምንኛ ባማረ ነበር። በምርጫ አለመሳተፍ ዋነኛ የትግል መንገድ መሆኑን ቆራጧ አንግ ሳን ሲኪ እያሳየች ነውና ከእሷ መማር ይቻላል ማለት ነው። በምርጫ አለመሳተፍ ትግል መሆኑን ከመቀበል ባሻገር ደግሞ በታይላንድ እንደሚታየው ህዝባዊ ተቃውሞን ማደራጀትም ይቻላል። የታይላንድና የኢትዮጵያ ሁኔታ አንድ አይደለም ማለቱ

ትክክል ቢሆንም በሀገራችንም አመቺውን ተቃውሞ ማድረግ የሚቻል ነው። ተቃዋሚ አይደለንም ተወዳዳሪ እንጂ፤ ሰላም ፈላጊ ነን ወዘተ በሚሉ መሸሸጊያዎች ተደብቆ ወያኔን በተጨባጭ/ በገቢር ማጀብ ግን ትግል ሊባል አይቻልም። በወያኔ ፓርላማ ተብዬ አዳራሽ መሳለቂያ መሆንና ሽፋን ሰጪነትም ከትግል አይፈረጅም። በምዕራብ አፍሪካ በቅርቡ ለምሳሌ በአይቮሪ ኮስት ድርጅቶች ሕዝብን ይዘው ባካሄዱት ትግል የምርጫውን ቦርድ አስቀይረው እንዲያውም የተቃዋሚዎች ድርጅት ተጠሪ በሊቀመንበርነት እንዲሰየምብት አድርገዋል። በሱዳንም በትግል በምርጫው ህግ ለዉጥ እውን ሆኗል። በነዚህ ሃገሮች ምርጫው ወደፊት አይጭበረበርም ማለት ባይሆንም ለፍትሃዊ ምርጫ አስፈላጊ የሆኑትን ለማሟላት ተገቢው ትግል ተካሂዷል ማለት ነው።

ወያኔን በተመለከተ ያለን የ19 ዓመት ተመክሮ ያስተማረንና አሁንም እያየን ያለነው ይህ ዘረኛ ቡድን የማይሻሻል ጸረ ህዝብ ሃይል መሆኑን ነው። ተቃዋሚ ሃይሎችን ደገፋችሁ በማለት ዜጎችን እየገደለ ነው። አፈናውን በሁሉም መስክ እያጧጧፈ ያለ መሆኑን ባዕዳን እንዲነግሩን አንፈልግም-- በበለጠ እኛው እናውቃለን። የግንቦቱን ምርጫ አሸናፊ ሆኖ መውጣቱ የተደመደመ ጉዳይ ነው። ለዚህም ነው በወያኔ ምርጫ አንሳተፍም ብንል ብቻውን ሮጦ አሸናፊ እንዲሆን ዕድል እንሰጠዋለን የሚሉት ክፍሎች የሚስቱት ይህንኑ ሃቅ ነው። ወያኔ ታጀበ አልታጀበ ብቸኛ አሸናፊ ሆኖ የሚገኝ ነውና ይህን ሃቅ ማጋለጡና ወያኔ ለብቻው ሮጦ (አምባገንን ነውና፤ የፍትሃዊ ምርጫን መንገድ ዘግቷልና) ብቸኛ አሸናፊ ሆነ ብሎ መሳለቂያ ማድረጉ ተመራጭ ነው። ሰሚ ቢኖር፤ የህዝብን ጥቅም መዘንጋት ባይቀድም ኖሮ። መለስና ስብሃት ነጋ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ያላቸው ጥላቻ የሚታወቅ ነው። በተለይም አማራውና ኦሮሞውን ህዝብ በጥላቻና ይህ በወለደውም ንቀት ማየታቸው የሚደበቅ አይደለም። አማራውና ኦሮሞው በተለይ የሃላፊነት ቦታዎች ላይ በርከት እንዳይል የሚል ውስጣዊ መመሪያ አለ ። ይህም የሚያመለክተው በምርጫ ወያኔ አማራና ኦሮሞ የሚላችው ድርጅቶች በምንም ዓይነት አሸናፊ ሆነው እንዲመጡ አይፈቅድም።

ስለዚህም ከበርማዋ ጀግና እንማራለን ካልን በወያኔ ምርጫ አለመሳተፍ ነው አማራጫችን። ከታይላንድና ሌሎች ህዝቦች እንማራልን ካልንም ህዝባዊ ኣመጽና ተቃውሞን ማፋፋም ነው ተልዕኮአችን ሊሆን የሚገባው።

ከራሳችን ከ1997 ኣኡ ተመክሮ እንማር ካልን ደግሞ ከ200 ህይወት በላይ የገበርንበትና ዛሬም ብዙ ሺዎችን ለእስር የዳረግንበት ነውና ወያኔን በትግል መጣል እንጂ ወያኔን በይስሙላ ምርጫው ማጀብ ተግባራችን ሊሆን አይገባውም።